በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
**The Federal Democratic Republic of Ethiopia**
**Ministry of Finance and Economic Development**

ቁጥር 7/ኢ/113/368
Ref. No.

ቀን 07 ጥቅምት 2007
Date

የዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት
የገቢ ቁጥር ...2.1/35
ቀን 11/02/2007

ለፌዴራል የዋናው ኦዲተር መ/ቤት
<u>አዲስ አበባ፣</u>

ጉዳዩ፣ <u>መመሪያዎችን ስለማሳወቅ፣</u>

1. ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም. በቁጥር ገ/ኢ/1/2/19 በተፃፈ ደብዳቤ ሸኚነት ለመንግሥት መ/ቤቶች የተላከውን <u>"የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ"</u> ሁለት ገጽ፣

2. ሐምሌ 01 ቀን 2006 ዓ.ም. በቁጥር ገ/ኢ/1/2/36 በተፃፈ ደብዳቤ ሸኚነት ለዩኒቨርስቲዎች የተላከውን <u>"የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ"</u> አምስት ገጽ፣

ለአፈፃፀም እንዲረዳችሁ ከዚህ ጋር አያይዘን የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አለማየሁ ጉጆ
ሚኒስትር ዴኤታ

ስልክ
TEL 251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 81, 83, 86, 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O. Box 1905, 1037
ፋክስ
Fax. 251-11-155 13 55, 55 14 96
251-11-155 38 44
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን
<u>ለማሻሻል የወጣ መመሪያ</u>

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መመሪያው እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

፩. የአንቀጽ ፲፯.፲፬.፪ (ሀ)፣(ለ)፣(ሐ) እና (መ) ተሰርዘው በሚከተሉት ንዑስ አንቀፅ (ሀ)፣ (ለ)፣(ሐ) እና (መ) ተተክተዋል፡፡

"ሀ. በውል ስምምነቱ መሠረት የግንባታ ሥራውን ለማጠናቀቅ ከአስራ ስምንት ወራት እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነት ጊዜ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ ከስድስት ወራት በላይ የሚፈጅ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣

ለ. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መነሻ እና የተሰወጠ ወቅታዊ ዋጋ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚሰጥ ሲሆን፣

ሐ. የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግበት በሚመረጠው ስብስብ ላይ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የዋጋ ኢንዴክስ ወይም የጠቋሚ ዋጋ መረጃ መስጠት መቻሉ ሲረጋገጥ፣

መ. በንዑስ አንቀጽ ፲፯.፲፬.፪(ሐ) የተገለጸው ቢኖርም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ መረጃ መስጠት ባልቻለባቸው ስብስቦች ላይ የመንግሥት መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ይገባል ብሎ ሲያምን ለውጥ የሚደረግባቸውን ስብስቦች በያዘው ምድብ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል የዋጋ መረጃ ከታወቀ የአገር ውስጥ አምራች ድርጅት ወይም በውጭ አገር ከሚገኝ ሕጋዊ ተቋም ማግኘት ሲቻል ፣"

፪. ከአንቀጽ ፲፯.፲፬.፪ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፯.፲፬.፫ ተጨምሯል፡፡

“ <u>፲፮.፲፬.፫ የዋጋ ማስተካከያ መረጃን ስለማቅረብ</u> ፤

ሀ. የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ለዋጋ ማስተካከያ መሠረት የሚሆኑ የተለያዩ ግብዓቶችን ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃ አዘጋጅቶ በየሶስት ወሩ መረጃውን ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

ለ. ኤጀንሲው ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ እና ከሌሎች የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የመረጃ ምንጮች የሚገኙ ወቅታዊ የዕቃዎችን ዋጋ የግዥ ሕጉን ለማሻሻል ለሚደረጉ ጥናቶች እንዲውሉ መሰብሰብና ማጠናቀር አለበት፡፡”

፫. ከአንቀጽ ፲፮.፲፬.፫ እስከ ፲፮.፲፬.፲ ያሉት ንዑሳን አንቀጾች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፲፮.፲፬.፬ እስከ ፲፮.፲፬.፲፩ በሚል ተስተካክለዋል፡፡

፬. በአንቀጽ ፲፮.፲፬.፭ ንዑስ አንቀጽ (ሀ)፤(ሐ) እና (መ) ላይ የሚገኘው “ ኤጀንሲው ወይም....” የሚለው ሀረግ ተሰርዟል፡፡

፭. አንቀጽ ፳፰.፭(ሀ) ተሠርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ተተክቷል፡፡

“ሀ. ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈፀመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ ይሆናል፡፡ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ ወደ ግንባታነት ላልተሰወጡ በግንባታ ቦታ ላይ ለሚገኙ የግንባታ ግብዓቶች (Material on-Site) ክፍያ መፈፀም አይቻልም፡፡”

፫. <u>ማሻሻያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ማሻሻያ ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰሌ 20 ቀን 2006 ዓ.ም.

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር

Memery/HB/TA

# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ
# አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገቢ የማመንጨት፤ የመጠቀምና የማስተዳደር ሥርዓት ወጥ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆንና ይህንንም የሚመራ የፋይናንስ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

ሀገራችን ያላትን ውሱን የፋይናንስ ሀብት ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መጠቀምን አስፈላጊነት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተምሣሌት ሆነው እንዲወጡ የሚያደርግ አሰራር ስራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፣

ይህ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ወጥቷል።

1. **አውጪው ባለስልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ከፍተኛ ትምህርት ተቋም" ማለት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው።
2. "የውስጥ ገቢ" ማለት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተልእኮአቸውን በማሳካት ሂደት ከሚያከናውናቸው ተጓዳኝ የሆኑ የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚሰበሰቡት የዕቃ ወይም የአገልግሎት ክፍያ ነው።

3. "መደበኛ ያልሆነ ተግባር" ማለት በመደበኛ ሁኔታ ከሚከናወን የመማር ማስተማር ተግባር፣ የማኅበረሰብና የምክር አገልግሎት፣ የጥናት እና ምርምር ሥራ ውጪ የሆነ በከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሚከናወን ተጓዳኝ የሆነ የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡

4. <u>የውስጥ ገቢ ምንጮች</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

- ከማታ ትምህርት ፣ ርቀት ትምህርት፣ ክረምት ትምህርትና እና መደበኛ ያልሆኑ ተማሪዎች ከማስተማር የሚገኝ ክፍያ፣
- አጫጭር ስልጠናዎች /የሙያና የክህሎት ሰርተፊኬት የሚያስጡ ሥልጠናዎች/ ከመስጠት የሚሰበሰብ ክፍያ፣
- መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት በውል ከሚደረግ ጥናት የሚገኝ የአገልግሎት ክፍያ፣
- ለአካባቢው ማህበረሰብ ከሚሰጥ የጤና አገልግሎት ክፍያ /ሕክምና፣ መድኃኒት ሽያጭ፣ ላቦራቶሪ ወዘተ.../
- መንግሥት ወይም መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት ከሚሰጥ የማማከር አገልግሎት ክፍያ፣
- መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሠራተኞች ለመለየት በውክልና ከሚሰጥ ፈተናና ተጓዳኝ አገልግሎቶች የሚገኝ ክፍያ፣
- ለኮንትራክተሮችና ሌሎች ተቋማት ከሚሰጥ የአፈር፣ ብረትና ሌሎች ግብዓቶችን ጥራት ለማረጋገጥ ከሚደረግ ናሙና ምርመራ ክፍያ፣
- ለዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ /ሠራተኛ እና ተማሪ/ ግልጋሎት የተቋቋሙ መዝናኛዎች ካፌቴሪያ፣ ስፖርት ማዘውተሪያዎች፣ ሬስቶራንቶች፣ ወዘተ የሚገኝ ገቢ፣
- ለዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ከተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች (ኮሚኒቲ ት/ቤት) የሚገኝ ገቢ፣
- ለዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ግልጋሎት ከተቋቋሙ መደብሮችና መጻህፍት መሸጫ ማዕከላት የሚገኝ ገቢ፣
- በዋናነት የተቋማትን አካዳሚያዊ እና የምርምር ሥራዎችን ለማተም የተቋቋመ ማተሚያ ቤት ከውጭ ተጠቃሚዎች የሚገኝ የአገልግሎት ክፍያ፣

- ከመማር ማስተማር፣ምርምር፣ ማህበረሰብ አገለግሎት ወይም ተቋም አስተዳደር ጋር ተዛማጅ ከሆኑ ሕጋዊ እንቅስቃሴዎች የሚገኝን ገቢ ያጠቃልላል፡፡

## 5. የውስጥ ገቢ አስተዳደር

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ በሚከተለው አኳኋን ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

### 1. በበጀት ዓመቱ ቀጣይነት ከሌላቸው እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች

የአንድ ጊዜ ወይም ደራሽ ከሆኑና ሲታቀዱ ከማይችሉ ሥራዎች ከሚገኝ የውስጥ ገቢ ውስጥ የእነዚህን ሥራዎች ሙሉ ወጪ ሸፍኖ የሚገኝ ተራፊ ገንዘብ በከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ ፕሬዚዳንት ሲፈቀድ መደበኛ ሳልሆኑ ተግባራት ሊውል ይችላል፡፡

### 2. በበጀት ዓመቱ ቀጣይ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች አጠቃቀም

ከዓመት ወደ ዓመት ቀጣይ ከሆኑና ሲታቀዱ ከሚችሉ ሥራዎች የሚገኘው የውስጥ ገቢ፡-

ሀ/ የውስጥ ገቢ መጠን እንዲሁም ገቢውን ለማመንጨት የሚወጣው ወጪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ቦርድ ይወሰናል፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል "ሀ" ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተገኘው የገቢ መጠን የገቢ ማስገኛ ሥራዎቹን ሙሉ ወጪ ሸፍኖ ተራፊው ገንዘብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከአመታዊ የበጀት ጥያቄ ጋር አቅርበው የውስጥ ገቢው በመንግስት ሲታወጅ ለፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

ሐ/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተስማሚ የስራ አካባቢን ለመፍጠርና ተልዕኮአቸውን ለማሳለጥ ካቋቋሟቸው እንደ መዝናኛ ማዕከላት፣ የተማሪዎችና ሠራተኞች መዝናኛ ክበባት፣ ጂም፣ ሪስቶራንት፣ የኮሚዩኒቲ ት/ቤቶች ፣የመጻህፍት ማዕከላት፣ የማተሚያ ቤቶች፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበረሰብ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ መደብሮች እና ተመሳሳይ ተቋማት የሚገኘው ተራፊ ገንዘብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ የሥራ አመራር ቦርድ በሚያጸድቀው መሰረት ለተቋማቱ አገልግሎት መስጫ ማስፋፊያና ማጠናከሪያ እንዲሁም ለሌሎች የሥራ አመራር ቦርዱ ለሚወስናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

3. <u>የፋይናንስ አስተዳደር</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢን ጥቅም ላይ ማዋል የሚችሉት ፀንተው የሚሠራባቸውን ሕጐችና መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

4. <u>የውስጥ ገቢን መጠቀም የማይቻልባቸው ሁኔታዎች</u>

ሀ/ በመንግስት ውሳኔ የተሰጠባቸው እንደየተማሪዎችና የህሙማን የምግብ በጀት ተመን ለመሳሰሉት ወጪዎች ከውስጥ ገቢ ከተመን በላይ መጠቀም አይቻልም፡፡

ለ/ የውስጥ ገቢን በመጠቀም ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር ተሽከርካሪ መግዛት አይቻልም፡፡

6. <u>የደረሰኝ አጠቃቀም</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 5(1) እና (2) የተዘረዘሩ የውስጥ ገቢዎችን መሰብሰብ የሚችሉት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲያሳትሙ በሚፈቀድላቸው ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ብቻ ነው፡፡

7. <u>የባንክ ሂሳብ</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለውስጥ ገቢ መሰበሰቢያ በሚፈቅድላቸው የባንክ ሂሣብ ብቻ መጠቀም አለባቸው፡፡

8. <u>የሂሳብ አያያዝና ኦዲት</u>

1. ለውስጥ ገቢ ራሱን የቻለ የሂሳብ መዝገብ መቋቋምና እያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ሂሳብ መደብ ተለይቶ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡
2. የውስጥ ገቢ ሂሳብ በአመቱ መጨረሻ ተዘግቶ በውጭ ኦዲተር መመርመር አለበት፡፡
3. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተመረመረ የኦዲት ሪፖርት በደረሳቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ አለባቸው፡፡

4. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ኦዲት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) በተደነገገው መሰረት የውስጥ ገቢን አጠቃቀም በተመለከተ እንደ አንድ መደበኛ አሰራር በየጊዜው ኦዲት ማድረግና አፈጻጸሙን ለተቋማቱ የበላይ ኃላፊ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## 9. <u>የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የበላይ ሀላፊዎች የውስጥ ገቢ አስተደደርን በተመለከተ ተገቢ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ስርአት የመዘርጋትና ተግባራዊነቱን የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 10. <u>ተፈፃሚ ያለመሆን</u>

የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 66 እና 67 መሰረት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚያቋቁሟቸው ኢንተርፕራይዞች በሚገኘው ገቢ አጠቃቀም ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 11. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 01 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ሐምሌ 01 ቀን 2006 ዓ.ም*

*ሱፍያን አህመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት*
*ሚኒስትር*